መልእክት ሁለት

**ወደ መለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛው ጫፍ መድረስ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ጢሞ. 1፥4፤ ኤፌ. 1፥10፤ 3፥9፤ ሮሜ 1፥3-4

**I. በእግዚአብሔር የተሰጠን የመለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛው ጫፍ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መገለጥ ነው—ሰው በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔርን ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ሰው መሆኑ፦**

ሀ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መብራራት የሆነው መላው መጽሐፍ ቅዱስ በሁለቱ የዘላለም ክፍሎች ውስጥ እና በጊዜ ድልድይ ላይ የሚታየው የሦስታንዱ አምላክ የግል የሕይወት ታሪክ ነው፦

1. ሦስታንዱ አምላክ ከዘላለም ወደ ጊዜ ውስጥ መጣ፣ ፍትሃዊ ቤዛነቱን ለመፈጸም በአራቱ ወንጌላት እንደታየው በሰው ውስጥ ላለው ቀጥተኛ እንቅስቃሴው *ሥጋ* የለበሰው አምላክ ለመሆን ወደ ስብዕና ውስጥ ለመግባት ከመለኮትነቱ ጋር መጣ—ዮሐ. 1፥14፣ 29።
2. ሕይወታዊ ማዳኑን ለማከናወን በሐዋርያት *ሥራ* እና በመልእክቶች የሚታየው በትንሣኤ የተቀመመው አምላክ፣ “በሂደት ያለፈው” አምላክ፣ ሁሉን-ያካተተው ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ—ዮሐ. 1፥32፣ 42፤ 1 ቆሮ. 15፥45፤ ፊልጵ. 1፥19።
3. በወደፊት ዘላለም በራእይ 21 እና 22 የሚታየው ብዙዎች የተካተቱበት አምላክ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ይሆናል።
4. በሂደት ያለፈው እና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ዳግም ከተወለዱት፣ ከተለወጡትና ከከበሩት አማኞች ጋር አጽናፍ-ዓለማዊው፣ የመለኮት-ስብዕና መካተት [መሆኑ] የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ግብ ነው—ዮሐ. 1፥51፤ ራእ. 21፥3፣ 22።
5. የእግዚአብሔር እና የጌታ ምለሳ ማዕከላዊ መገለጥ እግዚአብሔር *ሥጋ* መሆኑ፣ *ሥጋ* ሕይወት-የሚሰጠው መንፈስ መሆኑ እና የክርስቶስ አካል የምትሆነውን እና በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የምትጠናቀቀውን ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት ሕይወት-የሚሰጠው መንፈስ ሰባት እጥፍ ያየለ መንፈስ መሆኑ ነው።

ለ. ሰው በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔርን ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ሰው መሆኑ የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጠ-ነገር፣ በመጽሐፍ ቅዱስ “ሳጥን” ውስጥ ያለው “አልማዝ”፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ነው—ዘፍ. 1፥26፤ ዮሐ. 12፥24፤ ሮሜ 8፥29፦

1. እግዚአብሔር የሰውን ስብዕና በመካፈል በተሠግዎ በኩል ሰው ሆነ፤ ሰው የእግዚአብሔርን መለኮትነት በመካፈል በልውጠት በኩል እግዚአብሔር ይሆናል፦
   ሀ. የእግዚአብሔርን ሕይወት በመካፈል—ዮሐ. 3፥15፤ ቆላ. 3፥4።
   ለ. የእግዚአብሔርን ባሕርይ በመካፈል—ኤፌ. 1፥4፤ 2 ጴጥ. 1፥4።
   ሐ. የእግዚአብሔር አእምሮ በመካፈል—ኤፌ. 4፥23፤ ፊልጵ. 2፥5።
   መ. የእግዚአብሔርን ማንነት በመካፈል—2 ቆሮ. 3፥18፤ ኤፌ. 3፥8።
   ሠ. የእግዚአብሔርን መልክ በመካፈል—2 ቆሮ. 3፥18፤ ሮሜ 8፥29።
   ረ. የእግዚአብሔርን ክብር በመካፈል—ቁ. 30፤ ዕብ. 2፥10።
   ሰ. የእግዚአብሔርን ልጅነት በመካፈል—ኤፌ. 1፥5፤ ሮሜ 8፥23።
   ሸ. የእግዚአብሔርን መገለጥ በመካፈል—ቁ. 19።
   ቀ. የእግዚአብሔርን አምሳል ለመያዝ—1 ዮሐ. 3፥2።
   በ. የእግዚአብሔር ወገን—የእግዚአብሔር ዝርያ ለመሆን—ዮሐ. 1፥12፤ ሮሜ 8፥14፣ 16።
2. ይህ የመለኮት-ስብዕና የጥንዶች ፍቅር የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ርዕሰ-ጉዳይ፣ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ይዘት እና የመላው አጽናፍ-ዓለም ምሥጢር ነው—መኃ. 1፥1፤ 6፥13።

**II. የመለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ—በመጽሐፍ ቅዱስ “ሳጥን” ውስጥ ያለው “አልማዝ”—ሰው በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሰው የመሆኑ መገለጥ ነው—2 ሳሙ. 7፥12-14፤ ሮሜ 1፥3-4፤ ኤፌ. 3፥17፦**

ሀ. “እግዚአብሔር ሰው መሆኑ እና ሰው እግዚአብሔርን መሆኑ” የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ነው—1 ጢሞ. 1፥4።

ለ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ እግዚአብሔር በመገለጡ ይተልቅና ይስፋፋ ዘንድ መለኮታዊ ባሕርያቱ ሁሉ በሰው ሰናይ ባሕርያት እንዲገለጡ በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር ሰውን ልክ እንደ ራሱ ማድረግ እና ራሱን ከሰው ጋር አንድ ማድረግ፣ ሰውንም ከራሱ ጋር አንድ ማድረግ ነው—ኤፌ. 3፥9፤ 1፥10፦

1. የእግዚአብሔር በጎ ደስታ ከሰው ጋር አንድ መሆንና ሰውን በሕይወትና በባሕሪይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር ከራሱ ጋር አንድ ዓይነት ማድረግ ነው—ቁ. 5፣ 9።
2. እግዚአብሔር የራሱ ብዙ ርቢ እንዲኖረውና በዚህም አዲስን ወገን—አምላክ-ሰው ወገን—ለማፍራት ሰው ሆነ—ዮሐ. 1፥1፣ 14፤ 12፥24።

ሐ. ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም፣ እኛን በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔር ለማድረግ እግዚአብሔር ራሱን በክርስቶስ እንደ ሕይወታችን፣ ባሕርያችን እና ቅንብራችን ወደ ውስጣችን እንዲገነባ ያስፈልገናል—ኤፌ. 3፥17፤ ቆላ፣ 3፥4፣ 10-11።

መ. እግዚአብሔር በተሠገዎ ሰው ሆነ፤ ሰው ዳግም በመወለድ፣ በመቀደስ፣ በመታደስ፣ በልውጠት፣ በመምሰል እና በመክበር እግዚአብሔርን ይሆናል—ዮሐ. 3፥5-6፤ 1፥12-13፤ ሮሜ 6፥19፣ 22፤ 12፥2፤ 8፥29-30።

**III. የክርስቶስ አካል መፍራት የሚችለው ሰውን እግዚአብሔር ለማድረግ እግዚአብሔር ሰው በመሆኑ ብቻ ነው፤ ይህ ነጥብ በእግዚአብሔር የተሰጠን ራእይ ከፍተኛው ጫፍ ነው—ቁ. 3፤ 1፥3-4፤ 8፥14፤ 12፥4-5፦**

ሀ. የክርስቶስን አካል—ከፍተኛና የመጨረሻ መገለጧ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሆነችውን የሦስታንዱን አምላክ ሕይወታዊ አካል—ያፈራ ዘንድ ሰውን እግዚአብሔር ለማድረግ እግዚአብሔር ሰው ሆነ—ኤፌ. 1፥22-23፤ 4፥4-6፤ ራእ. 21፥2፣ 9-10።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ሰው የአምላክ-ሰው ኑሮ እንዲኖረው እንዴት እግዚአብሔርን መሆን እንደሚችል እና ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር ሕይወታዊ አካል እንደሚሆን ያሳየናል—ሮሜ 1፥3-4፤ 12፥4-5፦

1. ይህ ሕይወታዊ አካል እግዚአብሔር ሰውን እግዚአብሔር ለማድረግ ራሱን ከሰው ጋር ማጋጠሙና ማዋሐዱ ነው።
2. እግዚአብሔር ሰው የመሆኑ እና ሰው እግዚአብሔር የመሆኑ ውጤት ሕይወታዊ አካል ነው፤ ይህ ሕይወታዊ አካል የክርስቶስ አካል—የእግዚአብሔር ከሰው ጋር መጣመርና መዋሐድ ነው—ኤፌ. 4፥4-6፣ 12።

ሐ. እግዚአብሔር ልጁን የላከው ሰው እንዲሆንና በመለኮታዊው ሕይወት የአምላክ-ሰው ኑሮ እንዲኖር ነው፤ እንዲህ ያለው ኑሮ ከእርሱ ጋር ቁርጥ አንድ ዓይነት የሆነን አጽናፍ ዓለማዊ ሰውን—በመለኮታዊው ሕይወት የአምላክ-ሰው ኑሮ የሚኖር ከብዙዎች የሆነ አንድን ሰው ያመጣል—ሮሜ 8፥3፤ 12፥4-5።

መ. የክርስቶስ አካል እውነታ ከብዙዎች የሆነ አምላክ-ሰው በኑሮ እንዲገለጥ የእግዚአብሔር ከሰው ጋር መጣመርና መዋሐድ ነው—ኤፌ. 4፥4-6፣ 24።

© 2026 Living Stream Ministry